

አብረው የሚሰሩ የአውሮፓ አገሮች

# ጥገኝነት፣ ቤተሰብ መፈለግ እና መዘዋወር

→ አገርዎ ለእርስዎ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ከሆነ **ጥገኝነት መጠየቅ** ከፈለጉ፣ ለመኮንኖቹ ይንገሩ። አግባብነት ያለው ባለሥልጣን **እርስዎን ይመዘግባል**።

**በተመዘገቡበት አገር ይቆዩ።**

## በምዝገባ ወቅት መኮንኖቹ የሚከተሉትን ያደርጋሉ፡-

- ስምዎን፣ ዕድሜዎን እና ዜግነትዎን ይጠይቃሉ። ስለ ቤተሰብዎ እና እንዴት እዚህ እንደደረሱም ይጠይቃሉ።
- ፎቶዎን እና የጣት አሻራዎን ይወስዳሉ (ከ6 ዓመት በላይ ከሆኑ)።
- ሰነዶችዎን (መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ የልደት የምስክር ወረቀት) ይፈትሻሉ እና የእውቂያ መረጃዎን ይጠይቃሉ።

## የሚከተሉትን ከሆኑ ለመኮንኖቹ ይንገሩ፡-

- ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ እና ብቻዎን ከመጡ። እርስዎን እንዲደግፍ ሞግዚት የሚባል ሰው ይመድቡልዎታል።
- ቤተሰብዎን እየፈለጉ ከሆነ። ለርስዎ የሚበጀው ከሆነ፣ እንዲያገኟቸው ይረዱዎታል። ቤተሰብዎን መቀላቀል ካልፈለጉ ከሞግዚትዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ከዚህ በፊት ስለተቀመጡ ማንኛውም የአውሮፓ አገር የሚያውቁ ከሆነ።
- ደህና ካልሆኑ ወይም በአንድ ነገር ከተጨነቁ።



በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ በጣም ብዙ ሰዎች ወደዚህ አገር ከመጡ፣ አንዳንዶቹ **ወደ ሌላ የአውሮፓ አገር ሊዘዋወሩ ይችላሉ።**

**ለመዘዋወር የሚሄዱበትን** አገር መምረጥ አይችሉም።

በመዘዋወሩ ካልተስማሙ **ይግባኝ ማለት ይችላሉ**፣ ግን ምክንያትዎን ማስረዳት አለብዎት።

## ያስታውሱ

- ሁልጊዜ ምክር ለማግኘት ጠበቃ መጠየቅ ይችላሉ።
- ቋንቋውን መናገር ካልቻሉ አስተርጓሚ ይጠይቁ።
- እዚህ የሚሠሩ ሁሉም ሰዎች በአክብሮት ሊይዙዎት ይገባል።
- ከመኮንኖቹ ጋር ይተባበሩ። የሚናገሩት ነገር ግልጽ ካልሆነ ምን ማለታቸው እንደሆነ እንዲያስረዱዎት ይጠይቋቸው።



Amharic

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025